# ምድብ አንድ (የሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች)

## 30 ኛ ሳምንት

## የእመቤታችን ልደት

**ዓላማ**

- ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናት ድንግል ማርያም መወለድ መማር፡፡
- 

**ምንባብ**

- ስንክሳር ግንቦት 1

**መግቢያ**

- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናት ናት፡፡
- እግዚአብሔር እናቱ እንድትሆን የመረጣት ንጽሕት እና ቅድስት ስለነበረች ነው፡፡
- በዛሬው ትምህርታችንም ስለ ድንግል ማርያም ልደት እንማራለን፡፡

**ትምህርቱ**

- ኢያቄም እና ሐና የተባሉ ደጋግ ባልና ሚስቶች ልጅ ሳይኖራቸው ለረጅም ጊዜያት ይኖሩ ነበር፡፡
- ነገር ግን በእግዚአብሔር አምነው፣ትዕዛዘን ጠብቀው በጸሎት ይኖሩ ነበር፤
- ስለዚህም እግዚአብሔር ልጅ ሠጣቸው እግዚአብሔር ልጅ ከሠጣቸው፤እግዚአብሔርን እንዲያገለግል /እንድታገለግል/ እንደሚሠጡ ቃል ገብተው(ስዕለት ተስለው) ነበር፡፡
- ኢያቄም እና ሐና ልጅ ለመውለድ ከማይችሉበት ዕድሜ ደርሰው አርጅተው ነበር፡፡
- ለእግዚአብሔር የሚሣነው ነገር የለምና የእምነታቸውን ጽናት ተመልክቶ ቆንጆ ልጅ ሠጣቸው፡፡ ስሟንም ማርያም አሏት፡፡
- የተወለደችውም በግንቦት ነበር፡፡ ይሄንንም ቀን ልደታ ብለን እንጠረዋለን፡፡ ትርጉሙም “መወለድዋ” ወይም “ ልደትዋ ” ማለት ነው፡፡
- ኢያቄም እና ሓናን እግዚአብሔር በስተእርጅናቸው ቆንጆ ልጅ የሠጣቸው፣ ምክንያቱም ለፈጣሪያቸውና እርስ በርሳቸውም ታማኝነትስለነበራቸው፣ አመስጋኞች እና ተስፋ ሳይቆርጡ ልጅ እንዲሠጣቸው ይጸልዩም ስለነበር ነው፡፡

**ሙከራ**

1. የድንግል ማርያም አባት እና እናት ማን ይባላሉ?
2. ሐና እና ኢያቄም ለእግዚአብሔር ቃል የገቡት ምን ነበር?
3. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እና ማን ትባላለች?

**መዝሙር**

ምስራቀ ምስራቃት ሙፅዓ ፀሐይ
እግዝእትነ ዘመና ሙዳይ
ዘመና ሙዳይ ማርያም ዘመና ሙዳይ

# Virgin Mary with Baby Jesus



**ይቆየን፡፡**